በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም - ክፍል 4

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፲፪ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.**

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ ምሳሌዎች

- ምሳሌ የአንድ ነገር ማብራሪያና መግለጫ ሲሆን አንድ ነገር አማናዊ ሆኖ ከመምጣቱ በፊት የሚቀርብ ነው፡፡
- ጠቢቡ ሰሎሞን ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሯል፡፡ «እርሱም ሦስት ሺህ ምሳሌዎች ተናገረ፡፡» ፡፡ ***ቀዳ ነገ 4፡32፡፡***
- በሐዲስ ኪዳንም ስለ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ « በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም፡፡» ማቴ 13፡34፡፡ « መስማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር፤ ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም፥፡፡» ***ማር 4፡33፡፡*** ተብሎ ተጽፎልናል፡፡
- ምሳሌ ትርጉም ይሻል፡፡ « ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን፥ አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል፡፡» ***ማር 4፡12፣ ማቴ 13፡3-23፣ ማቴ 13፡36-43፡፡***
- በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተመሰሉ በርካታ ምሳሌዎች (የአቤል ደግነት፣ የኖኅ መርከብ፣ መልካም ርግብ፣ ቀስተ ደመና፣ የአብርሃም ድንኳን፣ በትረ አሮን…) ይገኛሉ፡፡ በርካታ ከሆኑት ምሳሌዎቿ መካከል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንመለከታለንለ፡፡

## ***የኖኅ መርከብ***

- ኖኅ ከጥፋት ውሃ ለመትረፍ መርከብ አዘጋጀ፡፡
- እርሱና ቤተሰቦቹ ከየወገኑም ከተመረጡት እንስሳት ጋር ወደ መርከብዋ ገብተው ተረፉ፡፡ ይህች መርከብ ዓለምን ያዳነውን የተሸከመች የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ ***ዘፍጥ 7፡2-23፣ ዕብ 11፡7፡፡***

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ ምሳሌዎች

***<u>ቀስተ ደመና</u>***

- «እኔም እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ፤ ከእናንተ ጋር ላሉትም ሕያው ነፍስ ላላቸው ሁሉ፥ ከእናንተ ጋር ከመርከብ ለወጡት ለወፎች፥ ለእንስሳትም ለምድር አራዊትም ሁሉ፥ ለማንኛውም ለምድር አራዊት ሁሉ ይሆናል። ቃል ኪዳኔንም ለእናንተ አቆማለሁ ሥጋ ያለውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም። እግዚአብሔርም አለ፦ በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥ ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው። ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ፥ የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል። በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች። በእኔና በእናንተ መካከል፥ ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ ሥጋ ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም።» ***<u>ዘፍጥ 9፡8-15።</u>*** እንደተባለው በሲኦል የነበረው የሰው ልጅ መከራ እንዲቀር እግዚአብሐየር ፈቅዶ ሰውን ለማዳን የመረጣት ነቢዩ ኢሳይያስ «ጌታ ምልክት ይሰጣችኋል..» ኢሳ 7፡14 ያለላት የቃልኪዳኑ ምልክት (ቀስተ ደመና) እመቤታችን ነች።

***<u>የአብርሃም ድንኳን</u>***

- «በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። ዓይኑንም አነሣና እነሆ፥ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፥ ወደ ምድርም ሰገደ፥እንዲህም አለ፦ አቤቱ፥ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ። ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፥ እግራችሁን ታጠቡ፥ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ፣ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፥ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና። እነርሱም፦ እንዳልህ አድርግ አሉት።» ***<u>ዘፍጥ 18፡1-5።</u>***
- እግዚአብሔር (ሥላሴ) በአብርሃም ቤት እንደተስተናገደ እመቤታችን በማኅፀኗ በትሕትና ተቀብላው ተስተናግዷልና እመቤታችን በአብርሃም ድንኳን ትመሰላለች።

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ ምሳሌዎች

## *የሲና ሐመልማል*

- « ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ሙሴም፦ ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ። እርሱም፦ እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው። ደግሞም፦ እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።» ***ዘጸአ 3፡1-6።***
- ሙሴ አንዱ ሌላውን ሳያጠፋው ሐመልማልና እሳት ተዋሕደው ነበልባሉ ሐመልማሏን ሳያቃጥላት ሐመልማሏ ነበልባሉን ሳታጠፋው አየ።
- ቅዱስ ቄርሎስና ቅዱስ ኤፍሬም እንደተናገሩት ነበልባሉ የመለኮት ወይም የጌታችን ሐመልማሉ የእመቤታችን ምሳሌ ናቸው። ጌታን በማኅፀንዋ ስትሸከመው አላቃጠላትምና።
- ቅዱስ ኤፍሬም በሐሙስ ውዳሴ ማርያም « ሙሴ በነደ እሳት ሳትቃጠል ያያት ዕፀ አንቺ ነሽ፤ ይኸውም መጥቶ በማኅፀንሽ ያደረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የመለኮትነቱ እሳትነት አላቃጠለሽምና።» ያለው ይህኑ ለማስረዳት ነው።

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ ምሳሌዎች

## *ጽላተ ሙሴ*

- ሙሴ እስራኤል የሚመሩበትንና አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽሙበትን ጽላት ከእግዚአብሔር እጅ ተቀብሎ ከሲና ተራራ ሲወርድ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ጥጃ ሲያመልኩ ተገኙ፡፡ ***ዘጸ 32፡1-ፍጻ እና ዘጸ 34፡1-ፍጻ፡፡***
- ጽላቱንም በጥጃው ላይ ጥሎ ጥጃውን አመድ አድሮጎ ጽላቱም ተሰበረ፡፡ ሌሎች ሁለት ጽላቶችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ አዘጋጅቶ ቢያቀርበው እግዚአብሔር ሕጎቹን ጻፈበት፡፡ ሕዝቡም በዚሁ ጽላጽ ጸመሩ፡፡
- የተሰበሩት ሁለቱ ጽላቶች በበደል ምክንያት የወደቁ የአዳምና የሔዋን ሁለተኛው የእመቤታችን ምሳሌ ነው፡፡
- በተሰበሩት ምትክ የእመቤታችን ምሳሌ የሆነው መሠራቱ በሔዋን ምክንያት የሞተው የሰው ልጅ ዳግማዊ አዳም ጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘባት በእመቤታችን ምክንያት የመዳኑ ምሳሌ ነው፡፡
- እስራኤል በሁለተኛው ጽላት እየተመሩ ምድረ ርስትን እንደወረሱ ክርስቲያኖችም ምክንያተ ድኂን በሆነች በእመቤታችን ምክንያትነት በተገኘው ድኅነት እየተመሩ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ፡፡ እመቤታችንም መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት የምንላት በዚሁ የተነሳ ነው፡፡

## *የታጠረች ተክል የታተመች ውሃ*

- «እኅቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት የተዘጋ ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት፡፡» መኃ 4፡12፡፡
- ገነት የተባለችው እመቤታችን ስትሆን፣ ተክል የተባለው ጌታችን ነው፡፡ አጥር የተባለው የእግዚአብሔር ረድኤት ነው፡፡

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ ምሳሌዎች

## *የታጠረች ተክል የታተመች የውሃ ምንጭ*

- በእመቤታችን በውስጧ ተተክሎ የነበረው ተክል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሷበረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቃ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ በንጽሕና በቅድስና አጊጣ በአሳብ፣ በመናገር በግብር ኃጢአት ሳይኖርባት ጌጻችንን ወልዳልናለች፡፡
- የተዘጋ/የታተመ የውሃ ምንጭ እመቤታችን፣ ከምንጩ የተገኘውም ውሃ ጌታችን ነው፡፡ ይህን ውሃም የተጠሙ ሁሉ ጠጥጠውት ረክተዋል፡፡ *ዮሐ 4፡7-15፡፡*

## *ስለ እመቤታችን የተነገሩ ትንቢቶች*

- አባቶች ነቢያትም በመንፈስቅዱስ ተመርተው ስለ እመቤበታችን በርካታ ትንቢታትን ተናግረዋል፡፡ ካል ጴጥ 1፡20-22፡፡

## ልበ አምላክ ዳዊት

- «የንጉሦች ሴት ልጆች ለክብርህ ናቸው በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች፡፡ ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዩ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥ እርሱ ጌታሽ ነውና፡፡ የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱላታል፡፡ የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ፡፡ በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተወለዱልሽ፥ በምድርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ፡፡ ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ ስለዚህ ለዓለምና ለዘላለም አሕዛብ ይገዙልሻል፡፡ » *መዝ 44፡1-17፡፡*

# ስለ እመቤታችን የተነገሩ

***ስለ እመቤታችን የተነገሩ ትንቢቶች***

**ልበ አምላክ ዳዊት**

- «ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።» ***መዝ 86፡6።***
- «ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ። እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም፥ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል።» መዝ 45፡4-5።
- «መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው ፤ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፥ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል። የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል።» ***መዝ 86፡1-3።***
- «የወደደውን የጽዮንን ተራራ። መቅደሱን እንደ አርያም ሠራ፥ ለዘላለምም በምድር ውስጥ መሠረታት።» ***መዝ 77፡68።***
- «እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፥ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና፥ እንዲህ ብሎ። ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ።» ***መዝ 131፡1-13።***

**ነቢዩ ኢሳይያስ**

- «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ***ኢሳ 7፡14።***
- «ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፥ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ።» ኢሳ 49፡23
- «የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፥ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ፥ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።» ኢሳ 60፡14።
- «እነሆ፥ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ።» ኢሳ 60፡2።

**ነቢዩ ሕዝቅኤል 44፡1-2**

# ወንድም የሚለው ቃል

- ወንድም የተለያዩ ፍቺዎችን አጠቃሎ የሚይዝ ነው፡፡ የሀገር ልጆች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ ሙሴ ጎበዝ በሆነ ጊዜ ወደ ወንድሞቹ ወጣ፥ የሥራቸውንም መከራ ተመለከተ የግብፅም ሰው የወንድሞቹን የዕብራውያንን ሰው ሲመታ አየ፡፡» ***ዘጸ 2፡11***
- በአንድ ቤተሰብ ያሉም ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ፡፡» ***ዘፍጥ 13፡8፡፡***
- የቅርብ ዘመዶች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « ሙሴም ከቃዴስ ወደ ኤዶምያስ ንጉሥ መልእክተኞችን እንዲህ ብሎ ላከ፡፡ ወንድምህ እስራኤል እንዲህ ይላል፡፡ ያገኘንን መከራ ሁሉ አንተ ታውቃለህ፡፡» ዘኁል 20፡14፡፡
- እውነተኛ ወዳጆች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « ወንድሜ ዮናታን ሆይ፥ እኔ ስለ አንተ እጨነቃለሁ በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበረ ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበረ፡፡» ***ካል ሳሙ 1፡26፡፡***
- የአንድ ነገድ ልጆች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ «ንጉሡም ዳዊት ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር ልኮ እንዲህ አላቸው፦ ለይሁዳ ሽማግሌዎች እንዲህ ብላችሁ ተናገሩአቸው፡፡ የእስራኤል ሁሉ ነገር ወደ ንጉሡ ደርሶአልና ንጉሡን ወደ ቤቱ ከመመለስ ስለ ምን ዘገያችሁ? እናንተ ወንድሞቼ፥ የአጥንቴ ፍላጭና የሥጋዬ ቍራጭ ናችሁ እናንተ ንጉሡን ከመመለስ ስለ ምን ዘገያችሁ? » ***ካል ሳሙ 19፡11-12፡፡***
- አንድ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « የኢዮሴዴቅም ልጅ ኢያሱ፥ ወንድሞቹም ካህናቱ፥ የሰላትያልም ልጅ ዘሩባቤል ወንድሞቹም ተነሥተው በእግዚአብሔር ሰው በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያቀርቡበት ዘንድ የእስራኤልን አምላክ መሠዊያ ሠሩ፡፡» ***ዕዝራ 3፡2፡፡***
- ቃል የሚገባቡ ሰዎች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ « እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ምርኮኞችን ሁሉ ለኤዶምያስ አሳልፈው ሰጥተዋልና፥ የወንድሞችንም ቃል ኪዳን አላሰቡምና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የጢሮስ ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም፡፡» ***አሞ 1፡9፡፡*** በሃይማኖች አንድ የሆኑ ሰዎች ወንድሞች ይባላሉ፡፡ ***ሮሜ 1፡3፣ ፊል 1፡12፣ ፊል 3፡1፣ ፊል 4፡1፣ ቀዳ ጢሞ 5፡1፡፡***

### የሚነበቡ መጻሕፍት

1. ወላዲተ አምላከክ በኢትዮጵያ፤ አለቃ አያሌው ታምሩ። 1979 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
2. ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ፤ ዲያቆን እሸቱ ታደሰና ዲያቆን ደጀኔ ሺፈራው። 1987 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
3. ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት፤ መምህር አንዱዓለም ዳግማዊ። 1998 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
4. ምልዕተ ጸጋ፤ ዓባይነህ ካሴ (ዲ/ን)። ጥቅምት 2000 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
5. St. Mary in the Orthodox Concept, Fr Tadros Y. Malaty
6. The Holy Virgin St. Mary, His Holiness Pope Shenouda
7. The Orthodox Way, Timoty Ware
8. The Orthodox Church, Timoty Ware

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org